# በድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያዊን ሙስሊሞች ፌደሬሽን

## የአቋም መግለጫ

በድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያዊን ሙስሊሞች ፌደሬሽን ከዩናይትድ ስቴትስ፣ ከካናዳና ከአውሮፓ የተገኙ የሙስሊም ተወካዮችና የተከበሩ አዛውንቶች የተሳተፉበት  የሁለት ቀን ሴሚናር ከDecember 09 እስከ 10, 2006 በዋሽንግተን ዲሲ አካሂደናል። አገራችን የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክቶ የሴሚናሩ ተሳታፊዎች ቀጥሎ ያለውን መግለጫ አውጥተናል።

ትኩረት ሰጥተን ከተወያየንባቸው ጉዳዮች መካከል በመስከረም/ጥቅምት ወር 1999 በጂማ፣ ኢሉባቦርና አካባቢው የተከሰተው አሳዛኝ ድርጊት፤ ከዚያም በማያያዝ “አክራሪ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን ጨፈጨፉ” በማለት የተደረገው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ አንዱ ነው። የተከሰተው ድርጊት ምንም አይነት ምክንያት ሊሰጠው የሚችል ባለመሆኑ በጽኑው እያዎገዝን በዚሁ አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተት የህይዎትም ኾነ የንብረት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን የተሰማንን ሃዘን እንገልጻለን።

ድርጊቱን ብቻ ማውገዝ በቂ ሆኖ ስላልታየን እንዴት እና ከየት ተነሳ የሚሉትን ለመረዳት ሁኔታውን በጥልቀት ለመመርመር ተገደናል።

ምንም እንኳን አሁን የተከሰተውን አይነት የሰውና የንብረት ጥፋት ባያስክትሉም በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜያቶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ እምነትን ተገን ያደረጉ ግጭቶችና የወንጀል ሰራዎች ተፈፅመዋል። ለምሳሌ ያክልም በተለያዩ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የእስልምና ሐይማኖት መመሪያ የሆነውን ቁርዓንን የማራከስ አጸያፊ ድርጊት ተፈጽሟል። የእስልምና የመጨረሻ ነቢይ በሆኑት ነቢዩ ሙሐመድ (ሱ.ዐ.ወ) ላይ የማንቋሸሽ ወንጀል ተደርጓል። መስጊዶች ለተደጋጋሚ ጥቃቶች ተዳርገዋል፣ ያለአግባብ ፈርሰዋል፣ ተቃጥለዋል። በተለይ በአክሱም ሙስሊሞች ላያ ያለው ድርብ ጭቆና እየተባባሰ መጥቷል።

እነዚህና ሌሎች በርካታ መሰል ችግሮች በወገናችን መካከል ቅራኔን፣ ጥላቻንና አለመቻቻልን የሚስያስከትሉ የወንጀል ሰራዎች እስካሁን ፍትህ ተችሯቸው በለጋነታቸው ባለመቀጨታቸው አገራችንን እና ህዝቧን በአደጋ አፋፉ ላይ እየጣሉት እንዳሉ ከዚህ በፊት ባወጣናቸው መግለጫዎች ገልጸናል[1]። አሁንም በጂማ/ኢሉባቦር የደረሰው የወገን እልቂት የጀመረው የመስቀል ዳመራ ምሽት በመስጊዶች ላይ በተሰነዘረ ጥቃትና ያንም ተከትሎ በተከሰተው ረብሻ የሙስሊም ወገኖቻችንን ህይዎት በማጥፋትና ሌሎችንም ለከፍተኛ ጉዳት በመዳረግ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ዝም ተብለው ሊታለፉ እንደማይገባቸው እናምናለን። ለእንደነዚህ አይነት ክስተቶችም ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች በጥልቀት ማጥናትና ወንጀለኞችንም ለፍርድ በማቅረብ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል። በጂማ/ኢሊባቦር

---

[1] http://www.ethiopianmuslimsfederation.com/Joint%20Statement.pdf
http://www.ethiopianmuslims.net/statements/statement%ethiomuslims_na$eu$ksa_210806.pdf
http://www.ethiopianmuslims.net/Forum/viewtopic.php?t=19

የተከሰተውንም አሳዛኝ ድርጊትና ከበስተጀርባው ያለውን ምክንያት ከሁለቱም እምነቶች የተውጣጣ አጣሪ አካል ወደቦታው በመሄድ ችግሩን ይመረምር ዘንድ እንጠይቃለን።

ከዚህም ጋር በማያያዝ ወንጀሉን ማን እንዳደረገው ምንም አይነት ተጨባጭና ተአመኔታ ያለው መረጃ ሳይያዝ ዘግናኝ የሆኑ ፎቶዎችን በቪድዮና DVD በማድረግ በቤተክርስቲያናትና በኢንተርኔት ሙስሊሞችን በጅምላ የሚኮንን ፕሮፓጋንዳ ማካሄድ ለችግሩ መፍትሄ ሆኖ ሰላም አምጭ ሳይሆን ለበለጠ ብጥብጥና ጥላቻ የሚጋብዝ በመሆኑ በጽኑው እናዎግዛለን። ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህን ህላፊነት የጎደለው ድርጊት ያወግዝ ዘንድም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ለዘመናት በዘለቀ የጭቆና ቀንበር ስር የኖረውን ኢትዮጵያዊ ሙስሊም እራሱን እንዳያውቅ፣ እምነቱን አውቆ እንዳይተገብር የሚፈልጉ ወገኖች የሙስሊሙን ህብረተሰብ መብትና ሊበረታታ የሚገባዉን የመንፈስ ተህድሶ “በአክራሪነት” መፈረጃቸው በጽኑው አሳዝኖናል፣ እያሳሰበንም ነው። ድርጊቱም በሙስሊሞች ላይ ይደረግ የነበረው ጭቆና እንዲቀጥልና ሙስሊሙን በእምነቱ ምክንያት ለማግለል ከሚደረጉ ጥረቶች ለይተን አናየዉም።

“ጂሃድስት”፣ “እስላሚስት” የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ አግባብነት የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ ትርጉማቸው በህብረተሰባችን ውስጥ በቅጥ የማይታወቁ ቃላቶችና አገላለጾችን መጠቀም ሙስሊሙን ህብረተሰብ በጂምላ የሚኮንና የህሌናም ሰላም የሚነሳ ሆኖ አገኝተነዋል። እነዚህ ነገሮች በማንኛዉም ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ትልቅ ጥንቃቄን የሚሹ በመሆናቸው ለዚሁ ገቢራዊነት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በአፍሪካ ቀንድ በተለይም በኢትዮጵያና በጎረቤት ሶማሊያ ማለትም አብዛሀኛውን የሶማሊያን ግዛት በተቆጣጠሩት የሶማሊያ እስላማዊ ፍ/ቤቶች መካከል ያለው ሁኔታ ሁለቱን አጎራባች አገሮችንና ህዝቦችን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ክልሉን አደጋ ላይ የሚጥል፣ መፍትሄ የማይገኝለት የፓለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ህይዎት ቀውሶችን ሊያስከትል የሚችል ኹኖ አገኝተነዋል። ችግሮችን በጦርነት ለመፍታት ማሰብ ነገሩን ከማካረርና ከማንወጣበት አዘቅት ከመዳረግ ሌላ ፋይዳ አይኖረውም። ከዚህ እውነታ በመነሳት ሁለቱም ወገኖች ለነገሩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ይፈቱ ዘንድ አበክረን እንጠይቃለን።

አላህ ለአገራችንና ለህዝባችን ሰላምን፣ እድገቱን፣ መግባባቱንና መቻቻሉን ይስጥልን።

በድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ፌደሬሽን

December 10. 2006
Washington DC.